# ከእግዚአብሔር ፍቅር

" ... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ፡፡" (ኢሳ 48 ÷ 17)

God's Love. P.O.Box 6734 . Lee's Summit. MO. 64064 አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ E-mail – glnlm@ethiogodslove.org

www.ethioGodslove.org 2ኛ ደብዳቤ 2006 እአአ 2nd Quarter 2006


ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ÷ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል፡፡ (ትንቢተ ኢሳይያስ 54÷13)



## ሽክምን ሁሉ አስወግዶ
### ወደ ፊት መሮጥ

ከብዙ ዓመታት በፊት፡በቤተ ክርስቲያናችን አንድ ችግር ነበረን፡፡ ይኸውም በዓመታት ውስጥ የተጠራቀሙ ዕቃዎችና ወረቀቶች ቤተ ክርስቲያናችንን ሞልተው፡ለአዲስ ሥራ ቦታ እስከናጣ ድረስ መጣበባችን ነበር፡፡ ጠረጴዛዎቻችን በወረቀት ክምር የተሞሉ ስለነበረ የተፈለገ ሰነድ ለቀናት አይገኝም ነበር፡፡

ከዚያም የተነሣ የቤተ ክርስቲያናችን ተግባራት ቅልጥፍና አልነበራቸውም፡፡ ይንን ሁኔታ ለማስወገድ ነበር ፡ እስከ ዛሬ ድረስ "ሽክምን የማራገፍ ቀን" ብለን የሰየምነውን የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓት የወሰንሁት፡፡

"በዚህ ሽክምን የማራገፍ ቀን" ብለን በሰየምነው ዕለት፡- የቤተ ክርስቲያናችን ዝግጅቶች በሙሉ ይሰረዛሉ፡፡ ሁላችን ሽራ ጫማ አርገን አሮጌ ልብስ ለብሰን÷ ትላልቅ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች አሰናድተን÷ በሺህ ኪሎ የሚቆጠር የወረቀቶችና የአሮጌ ዕቃዎች ጥርቃሞ እናስወግዳለን፡፡ ማንኛውንም ለቤተ ክርቲያናችን ዕድገት ሸክም ሆኖ የተገኘ ነገር እንጥላለን፡፡ጠቃሚ የሆኑትን ዕቃዎች ደግሞ ለቀልጣፋ ግልጋሎት በሚመች አኳኋን እናደራጃለን፡፡

በዚያንም ወቅት ሰው ነገሮችን መሰብሰብ እንጂ፡በየጊዜው የማያስፈልጉ ነገሮችን ከአስፋላጊዎች ለይቶ የማስወገድ ልማድ እንደሌለው ተረዳን፡፡ ስለዚህም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፡ በየጊዜው፡ ሁሉን ነገር አቁመን፡"ሽክምን የማራገፍ" ልማድ አደረግን፡፡ ጠቃሚነቱ የሚያጠራጥር ነገር ሁሉ እንደ ቆሻሻ ተቆጥሮ እንዲጣል የጽዳት ዘመቻ ቀን መርሆአችን ÷ መመሪያችን ነበር፡፡

በቅርቡ ባደረግነው "ሽክምን የማራገፍ" ቀናችን፡ ከጠረጴዛዬ ላይ ባራገፍነው የወረቀት ክምር አጠገብ ሳልፍ፡አንድ ነገር ወደ ልቤ መጣ፤ ይህንንም በጌታ መንፈስ ሆኜ እነግራችኋለሁ፡፡ ሰው ሁሉ በግለሰብ÷ በቤተሰብ ሆነ በማኅበር፡- ቆም ብሎ÷ በየጊዜው "ሽክምን ማራገፍ" ይገባዋል፡፡

በዚህ በምዕራቡ ሐገሮች የምንኖር ሰዎች÷ ቤታችንና ግቢያችንን፡ በየጊዜው እየሞሉ የሚያጣብቡ አላስፈላጊ ዕቃዎችንና ልብሶችን በየጊዜው ማራገፍ ያስፈልገናል፡፡ብዙዎቻችን ግን የጥንቱን ትዝታ ላለመልቀቅ ÷ አሁንም ወደ ፊትም የማይጠቅሙ÷ ነገሮችን ተሸክመን እንኖራለን፡፡

ስለ ሽክም ስንናገር፡- ልክ እንደ ቁሳዊው÷መንፈሳዊውም ሽክም ሊራገፍ እንደሚገባ ማሰብ ይገባል፡፡ የማይጠቅም ባሕሪይ÷ልማድ÷ተበዳይነት (ቅሬታ) ÷ መሠረት አልባ ምኞት ወዘተ መንፈሳዊ ሽክም ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

እኛ ክርስቲያኖች÷እግዚአብሔር የሰጠንን ራዕይ ይዘን፡ ወደ ተጠራንበት ግብ በሚገባ መገስገስ እንድንችል÷ በየወቅቱ ማራገፍ ያለብን ባሕሪያዊ ነገሮች ይኖሩናል፡፡ እነዚህም ነገሮች ÷ የምንማረውን የእግዚአብሔር ቃል በመጻረር በውስጣችን የሚኖሩ÷ገንቢ ያልሆኑ አስተሳሰቦችና የማያንጹ ልማዶች ናቸው፡፡ ማንኛውም ምዕመን ሕይወቱን ቢመረምር፡- በኑሮ ሆነ በአገልግሎት ወደ ኋላ ጎታች የሚሆን መወገድ የሚገባው ሽክም ይኖረዋል፡፡

በሩቅ ምሥራቅ ኤሲያ፡የዝንጀሮ ማጥመጃ አላቸው፡፡ ያም ምንም ያልተለፋበት ማሰሮ ነው፡፡ ማሰሮው አንገቱ ላይ ጠባብ ነው፡፡ በዚያም ዝንጀሮ ለማጥመድ የሚያስፈልገው፡ ጥቂት የቾሎኒ ፍሬዎች ብቻ በማሰሮው ውስጥ ማስቀመጥ ነው፡ ዝንጀሮው እጁን ማሰሮ ውስጥ ከትቶ ያቾሎኒውን እንዳፈሰ÷ እጁን ለማውጣት ሲቃጣ÷ከማሰሮው አንገት ጠባብነት የተነሣ÷ ይሳነዋል፡፡ ያቾሎኒውን ለቅቆ ከወጥመድ ማምለጥ ይችላል፡፡ ካልሆነ ግን ማሰሮውን ተሸክሞ ሲንገዳገድ ይያዛል

ለመጫወቻ ወይም ለእርድም ይወሰዳል:: አያሳዝንም?

ሰውስ እንዲህ ሊያዝ ይችላል? ያውም ክርስቲያን?ራሳችንን ቆም ብለን በመመርመር÷ አልላቀቅ ያሉንን ባሕሪያት ወይም ልማዶችን ልናስወግድ እንችላለን ፤ ከዚያም ከሚገባው በላይ እንደማይሸከም ሯጭ ÷ በትጋት ወደ ጌታ ዓላማ መገስገስ ይቀለናል::

“... <u>ሸክምን ሁሉ፡ ቶሎም የሚከብደንን ኃጢአት አስወግደን÷የዕምነታችንንም ተስፋና ፈጻሚውን እየሱስን ተመልክተን÷በፊታችን ያለውን ሩጫ በትእግሥት እንሩጥ፡ እርሱ ነውርን ንቆ፡በፊቱ ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ ፡ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና</u>”

(ዕብራውያን 12÷1-2)

ኮተት ተሸክሞ በእሽቅድምድም የሚሮጥ፡ ሸክሙን አራግፎ ቀልሎት በሚሮጥ ተወዳዳሪ መረታቱ ዕውቅ ነው:: የሚያሳዝነው ግን ብዙ ሰዎች በፈቃዳችን÷የማይረባንን ኮተት ተሸክመን ከሕይወት ሩጫ፡ ወደኋላ እንጎተታለን:: ወገኔ ሆይ ! የማይረባንን ሸክም እንጣል::

“በሩጫ ውድድር ሁሉም እንደሚሮጥና ከእነርሱ አንዱ ብቻ ሽልማት እንደሚቀበል ታውቁ የለምን? ስለዚህ እናንተም ሽልማትን ለመቀበል ሩጡ:: በሩጫ የሚወዳደሩ ሁሉ አድካሚ ልምምድ ያደርጋሉ፤እነርሱ እንዲህ የሚደክሙት የሚጠፋውንና ጊዜያዊ የሆነውን አክሊል ለማግኘት ነው::እኛ ግን የምንደክመው የማይጠፋውንና ዘላለማዊ የሆነውን አክሊል ለማግኘት ነው:: እኔ ግን ግብ እንደሌለው ሰው በከንቱ አልሮጥም ፤ ከነፋስ ጋር እንደሚታገል በከንቱ የምታገል ሰው አይደለሁም:: ስለዚህ ሌሎችን ወደ ውድድር ከጠራሁ በኋላ እኔ ራሴ ከውድድሩ ውጭ ሆኜ እንዳልገኝ ሰውነቴን እየተቆጣጠርሁ እንዲታዘዝልኝ አደርገዋለሁ::” (1ቆሮንቶስ 9÷24-27 ቀለል ባለ አማርኛ ትርጉም)

www.ethiogodslove.org

**በዚህ የድረ-ገጽ አድራሻ ከ2002 ዓም እ/አ/አ ጀምሮ የወጡ ደብዳቤዎቻችንን ማንበብ ሆነ አትሞ ማሰራጨት ይቻላል::**

የቅዱሳንን ሩጫ በሚገባ ለመሮጥ በየጊዜው የሚወገዱ ብዙ ነገሮች አሉ:: ሸክሞችን ባሰወገድን መጠን ሩጫው ቀለል ይላል:: ጌታም ሸክሜ ቀሊል ነው ያለው ሩጫ የሸክምን መቅለል እንደሚጠይቅ በማወቅ ነው፤ስሙ ይክበር:: በምድራዊውም ሩጫ ፡ ቀላል የሸራ ጫማ ይደረግና ግዴታ ካልሆነ በቀር ሌላ ምንም ሸክም አይጨመርም:: ብዙዎቻችን ግን ለሕይወት ሩጫ የማይጠቅሙ ሸክሞችን ባለማራገፍ፡በጫና ጎብጠን፡ እንኳን መሮጥ፡ መራመድም ብርቅ ይሆንብናል::

እዚህ ላይ ግን÷አንድ ጥንቃቄ ያስፈልጋል:: በአንዳንድ የሩጫ ዓይነቶች አስፈላጊ ሸክም አለ::

*በዱላ ቅብብሎሽ ውድድር ሯጮች ዱላ መሸከም ግዴታቸው ነው::* ***<u>ይህ የሕብረትም ሩጫ ነው:: ዱላው፡ተይዞ፡ በደምቡ ተሮጦ፡ የግልን ሩጫ ከጨረሱ በኋላ ፡- ለሚከተለው ሯጭ ማቀበልን ይጠይቃል</u>::***

እንዲህ ባለው ሩጫ፡ዱላ አለመሸከምም÷ከጣሉም አለማንሣት÷ በሥርዓት አለመሮጥም ÷ ሩጫውን አለመጨረስም÷ ከጨረሱ በኋላ ደግሞ ዱላውን ለተከታዩ ሯጭ አመቻችቶ አለማስተላለፍም ተሸናፊ ያደርጋል:: ሐዋሪያው ጳውሎስ የራሱን ሩጫ እንደፈጸመ ጽፎአል፡ ሩጫውም ከባድ ነበር:: ነገር ግን የሰላምን ወንጌል ለሚጠፉት የማዳረስ ሸክሙን እስከ መጨረሻው መሮጥ ነበረበት:: እኛም ከዚህ የተለየ ዕድል የለንም::

“ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከእየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ::

(የሐዋሪያት ሥራ 20÷24)

ወገኖቼ÷በሕይወት ጎዳና አስፈላጊ ነገሮችን የምንጥልበትና የማይጠቅሙ ነገሮችን የምንሰበስብበት ሁኔታ ይበዛል:: አንድ ጊዜ÷በአይሮፕላን እጓዝ ነበር:: ዳላስ አየር ጣቢያ ላይ አይሮፕላን ለመቀየር ወርደን ባለንበት፡“ሸክምን ማራገፍ” ታወሰኝ:: ወዲያውም ኪሶቼን ሞልተው ከነበሩት ÷ አይጠቅሙም ያልኳቸውን ወረቀቶች ሰብስቤ ቆሻሻ መጣያው ውስጥ ጨመርሁ:: ከዚያም በረራችንን ቀጠልን:: ትንሽም እንደ በረርን አንድ ጠቀም ያለቼክ ከቆሻሻ ወረቀቶች ጋር መጣሌ ታወቀኝ:: ቤቴም እንደ ደረስሁ ÷ ወደ ባንክ ደዋውዬ ቼኩ ዋጋ እንዳይኖረው ባላስደርግ ኖሮ÷ ደስ የማይል ነገር ፈጽሜ ነበር:: ከዚያም የተማርሁት “ሸክምን ከማራገፍ” በፊት የማይጠቅመውን ከጠቃሚው መለየት ጥንቃቄ የሚጠይቅ መሆኑን ነው::

<u>መራገፍ ያለበት መራገፍ ከሌለበት እንዴት እንለያለን?</u>

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ያስተምረናል::“ነገር ግን ይጠቅመኝ የነበረውን ሁሉ አሁን ለክርስቶስ ስል እንደ ጉድለት እቆጥረዋለሁ:: ከዚህም በላይ ለእርሱ ብዬ ሁሉን ነገር የተውሁለትን ÷ ወደር የሌለውን ጌታዬን ኢየሱስ ክርስቶስን ከማወቅ ታላቅነት ጋር ሳነጻጽር÷ ሁሉንም ነገር እንደ ጉድለት እቈጥረዋለሁ፤ ለእርሱ ስል ሁሉን አጥቼአለሁ፤ክርስቶስን አገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ፤ ሕግ በመጠበቅ የሚገኝ የራሴ ጽድቅ ሳይሆን÷በክርስቶስ በማመን ይኸውም ከእግዚአብሔር የሚመጣ

ከዕምነት በሆነ ጽድቅ በእርሱ ዘን ድ እንድገኝ ነው። ክርስቶስንና የትንሣዔውን ኃይል እንዳውቅ ፥ በሥቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞ ቱም እርሱን እንድመስል እመኛለ ሁ።" (ፊልጵስዩስ 3፥7-10)

እነሆ የእያንዳንዱ ምዕመን የሕይ ወት ግብ የተገለጠ ነው። ሐዋሪያ ው ጳውሎስ ይኸንኑ አስተምሮናል በአርአያነትም አሳይቶን አልፎአል እግዚአብሔር ይመስገን።

"ስለዚህ ርኩስነትንና ተንሰራፍቶ የሚገኘውን ክፋትን አስወግዳችሁ ነፍሳችሁን ማዳን የሚቻለውን፥በ ውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በትሕትና ተቀበሉ።"

(ያዕቆብ 1፥21 አ/መ/ት/)

የየራሳችንን ሩጫ በትጋት ለመሮ ጥና የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሕ ይወታችን ለማከናወን፥ ከወንድሞ ችና እህቶች ጋር ያለንን ግንኙነት ከጉድፎች (ከቅሬታዎች) ማጥራት (ማራገፍ) ግድ ነው። እንዲሁም ያ ለ ቅድስና እግዚአብሔርን ማየት ስለማይቻል ቅድስናን ለመጠበቅ ያልተቆጠበ የዕድሜ ልክ ጥረት መደረግ አለበት።

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል። "ከሰው ሁሉ ጋር በሠላም ለመኖር የሚቻላችሁን ሁሉ አድር ጉ፤ለመቀደስም ፈልጉ፤ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት አይችልም፤ ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጐድልበት ደግሞም መራራ ሥር በቅሎ ችግር እንዳያ ስከትልና ብዙዎችን እንዳይበክል ተጠንቀቁ።" (ዕብራውያን 12፥14)

ደግሞም "... ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚአብሔርንም በመፍ ራት ቅድስናችንን ፍጹም እናድር ገው።" (2 ቆሮንቶስ 7፥1) ሌሎ ችም መራገፍ ያለባቸው ሸክሞች አሉ። እነርሱንም መጽሐፍ እንዲህ ያስተምረናል። "አሁን ግን ቊጣን ንዴትን፥ስድብን፥ ሐሜትንና አሳ ፋሪ ንግግርን የመሳሰሉትንም ሁሉ አስወግዱ።" (ቆላስይስ 3፥8)

ወገኖቼ በዚህ ነገር በጽኑ ሊታሰብ በት የሚገባበት ምክንያት አለ። ቃሉ እንዲህ ይላል። "ዘመኑን በማ ስተዋል ይህን አድርጉ፤ከእንቅልፋ ችሁ የምትነቁበት ጊዜ አሁን ነው መዳናችን መጀመሪያ ከዳንንበት ጊዜ ይልቅ አሁን ወደ እኛ ቀርቦአ ልና። ሌሊቱ ሊያልፍ፥ቀኑም ሊጀ ምር ነው። ስለዚህ የጨለማን ሥ ራ ጥለን፥ የብርሃንን ጦር ዕቃ እን ልበስ። በጭፈራና በስካር አይሁን፡ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፤በክ ርክርና በቅናትም አይሁን። ይልቁ ንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ምኞቱንም ይፈጽም ዘንድ ለሥጋ በኃሳባችሁ አትመኙለት።" (ወደ ሮሜ ሰዎች 13፥ 13-14)

ጌታ ያላሸከመንን ሸክሞች ሁሉ አራግፈን፥እንደሚገባ አገልግለን፥ አክሊላችንን ከጌታ እጅ ለመረከ ብ እንድንበቃ ጌታ እግዚአብሔር ጸጋውን ያብዛልን። አሜን።

## እግዚአብሔርን የማወቅ ምስጢር




ከፈጣሪ ጋር በቅርበት መመላለስ

እያንዳንዱ ክርስቲያን፥ከአምላኩ ጋር እጅግ ተቀራርቦ መመላለስን ከሙሉ ልቡ ይመኛል ብዬ አምናለ ሁ። እንደዚሁም ፣ ኢየሱስ ጌታው የሆነ ሰው ሁሉ፥ከፈለገ፥ ይህንን የጌ ታ ቀርበት ሊያገኝ እንደሚችል ዕ ሙን ነው። ይህም በመጽሐፍ ቅዱ ስ የተደገፈ ነው።

ሆኖም የብዙዎቻችን ችግር አቀ ራረባችን ላይ ነው። ሁልጊዜ ወይ ም አብዛኛውን ጊዜ ጌታ ፊት የም ንቀርበው አቀፍ ሙሉ ልመናዎችን ይዘን ነው። ይህም ማለት እግዚአ ብሔርን መለመን የለብንም ለማለ ት አይደለም። እንዲያውም"...እር ሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስ ጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣ ሉት" ተብሎ ተጽፎአል። (1 ጴጥ ሮስ 5፥7)

ነገር ግን እግዚአብሔርን ማወቅና ከእርሱም ጋር ተቀራርቦ መመላለስ ከሚሹት፥ ጌታ መስማት የሚናፍቀ ው ፀሎት አለ። እርሱም ሙሴ እ ንደ ፀለየው ያለ ነው።

"አሁንም በፊትህ ሞገስን አግኝቼ እንደ ሆነ፡- አውቅህ ዘንድ፥በፊትህ ም ሞገስን አገኝ ዘንድ፥ መንገድህን አሳየኝ፥..." (ኦሪት ዘጸአት 33፥13)። በእኔ ግምት ከዚህ የተሻ ለ ፀሎት ያለ አይመስለኝም።

ሙሴ ጌታ ሆይ እባክህ ይህንና ያንን አድርግልኝ አላለም። "ጌታ ሆይ አንተን አውቅህ ዘንድ መንገድ ህን አሳየኝ" ነበር ያለው። ከዚያም ቀጥሎ በቁጥር 19 ላይ፡ "እባክህ ክብርህን አሳየኝ" እያለ ጸሎቱን ሲቀጥል እናነባለን። ጸሎቱም አል ተከለከለም፤ እግዚአብሔር ይመስገ ን።

"ክብርህን አሳየኝ" በሚለው ውስ ጥ፡ ክብር የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ትርጉም በጣም ጥልቅ ነው። ክብደት፥ መጠን ወይም ሁለንብ ማ ንነት ማለት ይሆናል።ስለዚህ ሙሴ እግዚአብሔርን የጠየቀው ማንነትህን በሙላት ልወቅ የሚል ነው። እንደ መልካም ወዳጆች በሚገባ ልወቅህ ና በቅርበት አብሬህ ልመላለስ ማ ለቱ ነው ።

ወገኖች፡- እንዲህ ያሉ ጸሎቶች የእግዚአብሔርን ልብ በፍቅር ይማርካሉ። ምክንያቱም እንዲህ ያሉ ጸሎቶች አይዘወተሩም።

ስለ ተወዳጁ የዩናይትድ ስቴትስ መሪ አብርሃም ሊንከን አንድ ታሪክ አነበብሁ። በወቅቱ በሐገሪቱ ውስጥ ጦርነት ይካሄድ ነበር። በዚያንም ጊዜ አንዲት ባልቴት ወደ ቤተ መንግሥቱ መጥታ፣ የያዘችውን ኩኪ የተባለ ጠፋጭ ምግብ በሳህን እንደታቀፈች ወደ ውስጥ ገብታ ተገኘች።

ከዚያም ባልቴቲቱ ፕሬዝዳንቱ ፊት እንድትቀርብ ተደረገ። እርስዋም እጅ ከነሣች በኋላ፡ "ፕሬዝዳንት ሆይ ! የመጣሁት አንዳች ልለምን አይደለም። ነገር ግን ይህንን ሐገር በዚህ ችግር ጊዜ ለመምራት ስላለብህ ሸክም ክብደት ሳስብህ ነበር። ስለዚህ እነዚህ የጋገርኋቸው ኩኪዎች ፊትህን ፈገግ ያረጋሉ ብዬ አስቤ አመጣሁልህ" አለችና ስጦታዋን አቀረበች።

ሁኔታው የፕሬዝደንቱን ልብ በጽኑ ነካ። እያለቀሱም፡- እንዲህ እያሉ መናገር ጀመሩ። "ወይዘሮ ሆይ በየዕለቱ በርካታ ሰዎችን አስተናግዳለሁ። ሁሉም እጅግ በርካታ ነገሮችን ከእኔ የሚፈልጉ ናቸው። ነገር ግን ፕሬዝደንት ከሆንሁ ጀምሮ ከጎበኙኝ ሰዎች ሁሉ መሐከል አንቺ ብቻ ከእኔ ለመቀበል ሳይሆን ለእኔ ለመስጠት አስበሽ መጥተሻል። እግዚአብሔር ይባርክሽ።"

እግዚአብሔር ልመናዎቻችንን ለመመለስ ደስ ይለዋል። ነገር ግን ወዳጆቹ ከሆንነው ሁሉ፡ የፍቅር መግለጫ መቀበልም ይናፍቃል። ለመሆኑ ለዚህ ሁሉን አትረፍረፎ ለሚሰጠን አምላክ፣ ከእርሱ ፈልገን ሳይሆን ፣ ፍቅራችንን ልንገልጽለት ብቻ ወደ እርሱ የምንቀርብ ስንቶቻችን እንሆን? እንደ ሙሴስ፡- "አውቀህ ዘንድ" እንዲሁ ከአንተ ጋር ለመቀራረብ ፣ ማንነተህን አሳምሬ አውቀ ዘንድ፣ "ክብርህን አሳየኝ" ብዬ ፊትህ መጣሁ የምንልበት ጊዜ ምን ያህል ነው?

ወገን ሆይ፡- ልክ እንደ ሙሴ እግዚአብሔርን በቀርበት ማወቅና አብሮ መኖር ይቻላል። እንደ ጳውሎስ እንደ አብርሃምም።ሐዋሪያው ጳውሎስ የሚከተለውን የጻፈው ለዚህ ነው። "እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ ፣ በመከራውም እንድካፈል፣ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፣ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ።" *(ፊልጵስዩስ 3፥11)*

አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር በቀርበት በመኖሩ በራዕይ ውስጥ ይኖር ነበር። "... አብርሃም ሆይ፣ አትፍራ፤ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ፤ ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው።" ያለውን የጌታ ድምጽ የሰማው በአምላኩ ቀርበት ውስጥ ሆኖ ነበር። (ኦሪት ዘፍጥረት 15፥1)

<u>የሕይወታችን ዕውነተኛ ዓላማ፡- እግዚአብሔርን ማወቅና ወዳጁ ሆኖ ሊሆን ይገባል።</u> ስለዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ ቢሆንም ባይሆንም የሚከተለውን ጸሎት አብረን እንጸልይ!

<u>ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ፡- አውቀህ ዘንድ፣ መንገድህን እባክህ አሳየኝ። ጌታ ሆይ፡- ብዙ ልመናዎች አሉኝ። በመጀመሪያ ግን የምለምንህ፡- ክብርህን እንድትገልጽልኝ ነው። አምላክ ሆይ፡- አንተን እንዳስደስት መንገድህን አሳየኝ፤አሚን።</u>

እንዲህ ያለ ጸሎት የጌታን ልብ ደስ ያሰኘዋል። ጌታም በእኛ ሲደሰት በሕይወታችን ውስጥ መገለጥ የሚጀምሩ ድንቆችና ተዓምራት ራሳችንንም ወገኖችንም ያደንቃሉ። ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲህ ያሉ የፍቅር ጸሎቶችን ከወዳጆቹ መስማት ስለሚናፍቅ ነው። ጌታ በልጁ ደም የዋጀን እንድናውቀውና በቀርበት አብረነው በመመላለስ እንድንኖር ነው። ክብር ለቅዱስ ስሙ ይሁን። አሚን።

# ምስጋና

*መጀመሪያ ይህንን አገልግሎት የሰጠንንና እናደርገውም ዘንድ ጸጋውን ያበዛልንን ጌታ እግዚአብሔር አምላካችንን እናመሰግናለን።*

እንደሁም በፀሎትና በማቴሪያል (በገንዘብና ጽሑፍ በማባዛት) የረዱንን ወገኖቻችንን፡ በጌታ በየሱስ ክርስቶስ ስም ተባረኩ እያልን ምሥጋናችንን እናቀርባለን።

- ወንድም ወንጌላዊ ሃሳቡ …… ………. ከያቨርላንድ ካንሳስ፡- መልክታችንን በማባዛት፡
- ወንድም ሰሙ መታፈሪያ ከካንሳስ ሲቲ፡ ሙዙሪ፡- በገንዘብ አስተዋጽዖ ከእኛ ጋር ስላገለገላችሁ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ።

## የዘላለም ሕይወት

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (የዮሐንስ ወንጌል 3÷16)

"ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና" (ወደ ሮሜ ሰዎች 5÷6)

"ኢየሱሰ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና ፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናል።" (ሮሜ 10÷ 9-10)

"መዳንም በሌላ በማንም የለም፡ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ፡ ከሰማይ በታች (ከጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) ሌላ የለምና። (የሐዋሪያት ሥራ 4÷12)

"በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ፡" (የሐዋሪያት ሥራ 16÷31)

የደኅንነት ፀሎት፡-

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡- ለዓለም ሁሉ ደኅንነት የተሰጠውን ኢየሱስን ጌታዬ አድርጌ እቀበላለሁ። ስለዚህ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ። ከዛሬ ጀምሮ በትምሕርቱ እኖራለሁ። ስለዚህ እንደ ተስፋ ቃልህ የዘላለም ሕይወት ወራሽ አድርገኝ ። ስለ ስምህ። አሜን።

## እየሱስ ጌታ ነው።
## ጌታ ይባርክህ።